# ግንቦት፣7

ከዚህ በታች ግንቦት 7በሚል ርእስ የማቀርበው አጨ.ር ግጥም መታሰቢ.ያነቱ የሀገራችንን ዳር ድንበርና አንድነት ለማስከበር ሲ.ሉ ዘምተው ከገንጣዮችና ከከፋፋዮች ሲ.ፋለሙ ለወደቁት ለታላቅ ወንድሜ ለወታደር ታጠቅ ፋንታዬ እንዲሁም ለሌላው ታላቅ ወንድሜ ልጅ ለመስፍን ስዩምና በተመሳሳይ ሁኔታ የሀገራቺንን ዳር ድንበርና ነጻነት ለማስከበር ሲ.ታገሉ ለወደቁ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በሙሉ ይሁንልኝ።

# ግንቦት፣7

በእለተ ስላሴ ሕዝቡ ታሪክ ሰርቱዋል፣
ፍትህ ዲሞክራሲ ነጻነቴን ብሉዋል።
ግንቦት ባይምሮዬ ሁሌም ይታወሳል፣
ታጠቅ ብሎ ዘምቶ ከገንጣይ ሲ.ፋለም፣
በግንቦት ሚካኤል የኔም ወንድም ወድቁዋል።
አውጥተናል እርም ከንግዲህ ምን ቀረን፣
ግንቦት 7 ደርሶ ሁሉን ካላሳየን።
እንዲሁ ተቀምጦ ቢ.ባል አቤት አቤት፣
እንደው በገዛ እጁ አይመጣም ነጻነት።
ፍትህ አይገኝም ከጨቁዋኝ፣ከዘረኞች ቤት፣
ትግል ነው መፍትሄው የሚያስገኝ ውጤት።
ሀገር ተቆረሰ ሕዝብም ተሰቃዬ፣
ግንቦት አልቻለውም ይህንን እያዬ።
ግፋ በጣም በዛ መጠኑን አለፈ፣
ይህን ከማይ ብሎ በግንቦት 7 ሰር ታጋይ ተሰለፈ።
እውቁ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰር መስፍን፣
ባንድ ወቅት እንዳሉን፣እንዳስገነዘቡን፣
ግፍ የሚበዛው ሲ.ያገኝ ነው ተሸካሚውን።
ግንቦት 7 ሲ.ደርስ ምንድነው ጨጨታው፣
ሕዝቡ እንደሁ ያውቀዋል የት እንዳለ እውነታው።
ለሀገር የምናስብ፣እየተመካከርን፣እየተባበርን፣
መናቆሩን ትተን አንድ ላይ በመሆን ሀገር እናድን።
ሽማግሌዎችም እውነት ተናገሩ፣
ድሮም ይባል ነበር ነገርን ከስሩ።
የሚከበር ነበር የሀገር ሽማግሌ፣
ወያኔ አበላሸው እያላሰ አሞሌ።
የወገን መበደል የሀገር መቆረስ፣
እልባት ያገኛል ግንቦት 7 ሲ.ደርስ።
በጣም ጠቃሚ ነው ካለፈው መማር፣
የግንቦት፣7-ም ትግሉ እንዲሰምር።
ሀገር እንደሌለው ብንከራተት፣
እንገናኛለን በግንቦት ሰባት።
ነጻ አውጪ ነኝ ብሎ የመጣን ለጥፋት፣
ቦታውን አሳየው የኛ ግንቦት ሰባት።
ግንቦት 2001(May 2009)
ይበልጣል እውነቱ ከጀርመን።